


ከዓለም ምግብ ፕሮግራም (WFP) እና ከCARE Denmark ጋር በመተባበር የተቋቋመው ኢግናይት የፈጠራ ውድድር በምስራቅ አፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና የአመጋገብ ችግሮች ላይ ለመስራት የተመሰረተ በአይነቱ የመጀመሪያው ማዕከል ነው። ዋና አላማው በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር እና በአካባቢው ማኅበረሰቦች የሚመራ ዘላቂ የምግብ አሰራርን መፍጠር ሲሆን፤ ማዕከሉ የአካባቢ ችግሮችን ለመፍታት፣ ስራ ፈጣሪነትን ለማጎልበት እና ተጽዕኖውን ለማስፋት ቁርጠኛ ነው።

ማዕከሉ ከWFP ETCO፣ Care Ethiopia እንዲሁም ከIceaddis ጋር በመተባበር በኢትዮጵያን የመጀመሪያውን የፈጠራ ፕሮግራም እያስጀመረ ይገኛል። የውድድሩ አላማ በምግብ ምርትና በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ ችግሮችን መፍታት የሚችሉ ስራ ፈጣሪዎችን መለየት ነው።

## 2. የማስታወቂያ ስራዎች

አጋሮች የውድድሩ ተሳታፊዎችን እንዲሁም የተቀበሏቸውን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣ በድረገጻቸው ላይ እና [አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ሁኔታ] በሌሎች የማስተዋወቂያ ጽሑፎች ላይ የማተም መብታቸው የተጠበቀ ነው። ተሳታፊዎች በተሳትፏቸው በማስተዋወቂያ እንቅስቃሴዎች፣ ዝግጅቶች እንዲሁም ጋዜጣዊ መግለጫዎች ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛና ዝግጁ እንደሚሆኑ፤ በተጨማሪም አዘጋጆቹ የተሳታፊዎችን ስም፣ ፎቶግራፎች እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን በሁሉም የሚዲያ መረቦች ከክፍያ ነጻ በሆነ መልኩ ለህዝብ ይፋ ማድረግ እንደሚችሉ ይስማማሉ።

## 3. የተሳትፎ ቅድመ ሁኔታዎች

መርሃ ግብሩ በአማራ እና አፋር ክልሎች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚሰሩ አዳዲስ ሀሳቦች/ምርት ላላቸውና በኢትዮጵያ ለሚገኙ ድርጅቶች ወይም ቡድኖች ነፃ እና ክፍት የሆነ መርሃ ግብር ነው።

ተሳታፊዎች ለተሳትፎ ብቁ ለመሆን በማመልከቻው ቀን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

- ኢትዮጵያ ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የተመዘገቡ እና የተቋቋሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድና ማስረጃ ያላቸው፣
- ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያላቸው፣
- ዝቅተኛው የመስራቾቻቸው ዕድሜ 18 ዓመት የሆነ፣
- የመርሃ ግብሩን ተግባራት ሙሉ በሙሉ መሳተፍ እና ማከናወን የሚችሉ፣ እንዲሁም
- በየዓመቱ ቢያንስ 200,000 ብር የሚሆን ገቢ እንደሚያገኙ ማረጋገጫ ያላቸው።

የሴት ሥራ ፈጣሪዎች እና በሴቶች የሚመሩ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተሳትፎ ይበረታታል።

በመርሃ ግብሩ በመሳተፍ፣ ተሳታፊዎች በደንብ እና መመሪያዎቹ መስማማታቸውን ያረጋግጣሉ።

## 4. ፍቺ/ትርጓሜ : ኢግናይት የአየር ንብረት ፈጠራ መርሃ ግብር

መርሃ ግብሩ ለምግብ ምርት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ መቋቋም እና ለተመጣጠነ የምግብ እጥረት መፍትሄ የሚሰጡ አዳዲስ ተሞክሮዎችን፣ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን እና የህብረት ስራ ማህበራትን ለመደገፍ እና ለማስተዋወቅ ያለመ ነው። በኢትዮጵያ የአማራ እና አፋር ክልሎች የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና የህብረት ስራ ማህበራት የአደጋ ተጋላጭ ማኅበረሰቦችን ፍላጎት ለማሟላት የተዘጋጁ ማመልከቻዎችን እንቀበላለን። እነዚህ አካላት በአየር ንብረት ለውጥ የተባባሱ ችግሮችን ለመቅረፍ በምግብ እና በከብት እርባታ፣ አቀነባበር፣ ስርጭት እና ስነ-ምግብ ዘላቂ መፍትሄዎችን በመፍጠር እና በመተግበር ላይ ማተኮር አለባቸው።

ሁሉም መፍትሔ አቅራቢዎች እንዲያመለክቱ ቢበረታቱም፣ በሚከተሉት ዘርፎች ለተሰማሩ ቅድሚያ ይሰጣል።

1. የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አቅምን ለማሻሻል
    - ዘመናዊ ልምዶችን የሚያስተዋውቁ።
    - ለምግብ ምርት፣ ማቀነባበሪያ፣ ማከማቻ እና ፍጆታ ንፁህ ሃይልን የሚጠቀሙ።
    - ለምግብ ምርትና ማቀነባበሪያ ቀልጣፋ የውሃ ተደራሽነት እና አጠቃቀምን የሚያስተዋውቁ።
2. የምግብ ምርትን፣ ሂደትን እና ስርጭትን ለማሻሻል
    - የመንግስትና የግል ሽርክናዎችን በማጠናከር በማኅበረሰቡ የሚመራ እና ዘላቂነት ያለው አካሄድ ያላቸው።
    - ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ፍላጎቶች የሚያስቀድሙ።
3. የአመጋገብ ችግሮችን ለመፍታት
    - የንጥረ ነገር እጥረቶችን ለመከላከል ቅድሚያ የሚሰጡ።
    - የባህሪ ለውጥ ላይ የሚያተኩሩ።
    - በሀገር ውስጥ የሚመረቱ አልሚ ምግቦችን የሚያሰተዋውቁ።
4. የአካባቢን ንፁህ የኃይል ምንጮችን እና ቀልጣፋ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም
    - የህብረተሰቡን የአገልግሎቶች፣ የምግብ እና የሃብት ተደራሽነትን እንዲሁም የግብይት እና የእርሻ ማቀነባበሪያ ስርዓቶችን ለማሻሻል የፀሐይ ሃይልን እና ዲጂታላይዜሽን መጠቀም።
    - ሀገር በቀል ቁሳቁሶችን እና የማምረቻ ቴክኒኮችን መጠቀም።
    - የማኅበረሰብ ተሳትፎን እና ልማትን በማጎልበት በወረዳ ደረጃ ጉልህ ተሳትፎን ማሳየት።

## 5. የማስረከቢያ ቀነ-ገደብ

የኢግናይት ፈጠራ መርሃ ግብር ማመልከቻ የማስረከቢያ ቀነ-ገደብ ሐምሌ 23፣ 2016 ዓ.ም ነው።

ማመልከቻዎች በ [https://www.iceaddis.com/ignitehubet-am/](https://www.iceaddis.com/ignitehubet-am/) ላይ በተጠቀሰው ቅጽ ወይም በአገር ውስጥ ባሉ የዓለም ምግብ ፕሮግራም እና CARE ቢሮዎች ሊቀርቡ ይችላሉ። አመልካቾች ቅጹን ወስደው ለተመረጡ (የአማራ እና የአፋር) ክልል ቢሮዎች ማቅረብ ይችላሉ። ማመልከቻዎቹ አስፈላጊ ዝርዝር መረጃዎችን በቅጹ ማካተት አለባቸው።

የምርጫ መስፈርት፡-

● ፈጠራ፡- የታቀደው የመፍትሄ ሃሳብ ነባር ጉድለቶችን የመሙላት አቅሙን ጨምሮ፣ የፈጠራው ደረጃ እና ልዩነት ይገመገማል።

● ተፅዕኖ፡- መፍትሔው በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ እና በተጠቀሱት ክልሎች ውስጥ ያሉ የምግብ ዋስትና ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ይገመገማል።

● አዋጭነት፡- የቀረበውን የመፍትሄ ሃሳብ የአተገባበር እንዲሁም ቴክኒካል አዋጭነቱን ጨምሮ መጠነ ሰፊነቱን እና የረዥም ጊዜ ዘላቂነቱ ይገመገማል።

● ከዓላማዎች ጋር መጣጣም፡ አተገባበሩ ከኢግናይት ፈጠራ ውድድር ግቦች እና አላማዎች ጋር እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ የምግብ ስርዓትን የማጎልበት አጠቃላይ ተልእኮውን ለማሳካት ካለው አቅም ጋር መጣጣሙ ይገመገማል።

● የአካባቢ አውድ፡ ሃሳቡ ምን ያህል የአካባቢ ሁኔታዎችን፣ ባህሎችን፣ ፍላጎቶችን እና የአካባቢ ችግሮችን ለመፍታት መፍትሄዎችን የመጠቀም ችሎታን ያሳያል የሚለው ይገመገማል።

## 5.1 የማመልከቻ ቋንቋዎች

አመልካቾች ማመልከቻቸውን በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ማቅረብ ይችላሉ።

## 5.2 ልዩ ድንጋጌዎች

የቀረቡት ተወዳዳሪ ፕሮጀክቶች ለዳኞች ከመቅረባቸው በፊት መስፈርቱን የሚያሟሉ መሆናቸው ይጣራል።

በቴክኒክ ችግሮች ምክንያት ዘግይተው ለሚቀርቡት ማመልከቻዎች አጋሮች ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም።

## 6. ምርጫ ዳኞች

የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምርጫ የሚከናወነው በአጋር አካላት በተመደቡ ዳኞች ነው።

- የመጨረሻ እጩዎቹ የሚመረጡት በጥብቅ የምርጫ መስፈርቶች ነው።
- የምርጫ ዳኞች እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች ባለሙያዎች ምክር እና መመሪያ የመጠየቅ መብት አላቸው። ይህም የተወዳዳሪ ፕሮጀክቶቹን ሐቀኝነት ለመገምገም እና የሶስተኛ ወገን የአእምሯዊ ንብረት መብቶችን የሚጥስ አለመሆኑን ማረጋገጥን ይጨምራል።
- የዳኞቹ ውይይት በሰነድ ተይዞ የመጨረሻው ውሳኔ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ይሆናል። ከዚህ ባሻገር እነዚህ ውሳኔዎች በተናጥል የሚከናወኑ ሲሆን፣ የበላይ እና ለክርክር የማይቀርቡ ናቸው።
- የምርጫ ዳኞች እና አባላት በማንኛውም የተመዘገበ ተሳታፊ ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን ማንኛውንም የግል ወይም የገንዘብ ፍላጎት፣ ለስፖንሰሮች ወይም ለኮሚቴ አባላት ማሳወቅ አለባቸው። ዳኞች ከተሳታፊ ወይም ከስፖንሰር ጋር የዝምድና ወይም የገንዘብ ግንኙነት ካላቸው፣ ከተሳታፊው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ከመገምገም ወይም ድምጽ ከመስጠት መቆጠብ አለባቸው።
- የመራጩ ዳኞቹ ውሳኔ የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይባል ነው።ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ https://www.iceaddis.com/ignitehubet-amን ይጎብኙ።